# ሰሞነኛ

## ገፅታን በማበላሸትና ባሉባልታ፣ የአገር እድገት አይገታ

በረጅሙ የአገራችን ታሪክ ለመረዳት እንደሚቻለው በተለያዩ ታሪካዊ ወቅቶች በልዩ ልዩ ምክኒያቶች ያለመግባባትና ግጭቶች ይከሰቱ እንደነበር የሚታወቅ ነው።ይሁን እንጂ አገራዊ ህልውናችን የሚፈታተን ጉዳይ ከውጭም ከውስጥም ሲነሱ ህዝባችን በአንድነት የመቆም ፣የመክተት፣የመዝመት፣ የመመከትና ለዚሁ ዓላማ የመሰዋት ታሪክ አለው።የጣሊያን መንግስት በዕብሪት ተነሳስቶ በሰሜኑ በኩል ድንበራችንን ተሻግሮ ወረራ ሲፈፅም በወቅቱ ስልጣን ላይ የነበሩት አፄ ሚኒሊክ የክተት አዋጅ ባወጁበት ወቅት ዘር፣ ጎሳ፣ሀይማኖት ሳይለይ በአንድ ተነስቶ አድዋ ላይ ይሄው እስከ ዛሬ እኛ ብቻ ሳንሆን መላው አፍሪካና ተጠቂ ህዝቦች የምንኮራበት ታሪክ ሊሰራ በቅቷል።ታዲያ በዚያ ጊዜ ሁሉም የኢትዮጵያ ማህበረ ሰብ አባላት እንዲሁም ማንነታቸው የተረገጠና የተናቀ የህዝባችን ክፍሎች የአገር ጉዳይ አንገት የማያሰቀረቅርና፣ ፊትን አዙሮ የማያስኬድ ሆኖባቸው በዚያች ቁርጥ ቀን ተገኝተው ከሁሉም በላይ ውድ የሆነችውን ህይወታቸውን ለዚች አገር ሊለግሷት በቅተዋል።በሞታቸውም እኛን አኩርተው አገራቸውን አስከብረዋል።ይህ ነው በኢትዮጵያዊነታችን የሚኮራን ውርስ!!

እኒሁ ቀደምት ወላጆቻችን በጦርነት ብቻ ሳይሆን በሰላምም ወቅት አገራችንን ያለ መልኳ መልክ ሊሰጧት የሞከሩትን፣የለም በማይሆን መንገድ አትምጡብን አሉ እንጂ! አገርን ለቅኝ ገዢዎች አሳልፈው አልሰጡም። ታድያ እኛስ ማነን? የወላጆቻችን በህሪያዊ ውርሶች፣ወይስ የሹመኝነት ናፍቆት በአዕምሮ ሙቅ ቀይዶ የያዘን የአገር ስም አጠቋሪዎች? አብዛኛው በውጭ የሚኙ ኢትዮጵዊ በሱማሌ በኩል አክራሪ ሃይሎች የህዝባችን ህልውና ለመፈታተን ሲነሱ በውጥኑ አንስቶ እነዚህ ሀይሎች አገራችን የጀመረችውን የዕድገት ትልም ለማኮላሸት ከጠላቶቻችን ጋር ተደራጂተው የመጡብን መሆናቸውን ጠንቅቆ በማወቅ ማንነታቸውን ለማጋለጥ ተንቀሳቅሷል። ኃላም መንግስትና የመከላከያ ሰራዊታችን በተከታታይ የሽብርተኛ ሀይሎችን አከርካሪ ሲሰብሩ በቁጭት ያረረው አንጀታቸው መራስ ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያዊነታቸው ቀና ብለው መራመድ ችለዋል። ከዚያም ወዲህ ሻብያ እያሰታጠቀ በሚልካቸው ጦፈኞቹ አመካኝነት የሚያካሂደውን የሽብር ተግባር በምሬት አውግዘዋል። ከሁሉም በላይ የኢትዮጵያ መንግስትና ገዢው ፓርቲ የጀመረውን ድህነትን ታሪክ የማድረግ ተጋድሎ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ከልብ ከመድገፍ በላይ ፣ ራሳቸው በኢንቨስትመንት ፣በንግድና መንግስታዊ ባልሆነ ድርጅት በሚያበረታታ መልክ በመሳተፍ ላይ ናቸው።



Bi-monthly news bulletin prepared by the Consulate General of Ethiopia
3460 Wilshire Blvd # 308 Los Angeles, CA 90010
Tel: 213 365 6651 Fax:213 365 6670 info@ethioconsulate-la.org
www.ethioconsulate-la.org

በሌላ በኩል ደግሞ በአገራችን በጎ ጎኖች አንዳችም አስተዋፅኦ ኖሯቸው የማያውቅ ጥገኛ ወገኖች ቀኝ ስንል ግራ፣ ወደፊት ስንል ወደ ኃላ፣ ኅብረት ስንል መነጠል፣መወያየት ስንል መናቆር፣ልማት ስንል ጥፋትን፣ዴምክራሲ ስንል አመፅን፣ነፃነት ስንል ስርዓት አልበኝነትን በመስበክና በማራመድ ረገድ ያረፉበት ጊዜ የለም::

ፅንፈኛ የተቃዋሚ ቡድኖች አገራችን ለመበታተንና ለማዳከም ጠላቶቻችን ተደራጂተው ሲመጡብን እነሱም ከነዚሁ ጎን በመቆም የአገራችን መከራ ለማራዘም ጥረዋል::አክራሪዎች በሚፈፅሙት የበላዔስብ ዲርጊት ከጠላቶቻችን ጋር አብረው በወገኖቻችን ሞት ተሳልቀዋል::ጠላቶቻችን አይቀጡ ቅጣት ስንቀጣም ድላችንን ከማጣጣል አልፈው ለጠላቶቻችን ተቆርቋሪ በመሆን የመከላከያ ሰራዊታችን ያመጣውን ድልና ገድል ለማራከስና ትቢያ ለማልበስ ጥረዋል::  እነዚህ ክፍሎች በውጭ የሚገኙ የተለያዩ ድጋፍ ሰጪ አካላት ለአገራችን የሚሰጡትን የልማትና የአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ እንዲቆምና የህዝባችን ጉሮሮ እንዲዘጋ ሲባክኑ ይስተዋላል:: ይሄው የርዳታ ከልክሉልን ተማፅኖ ሳይሳካ ሲቀር ደግሞ በነዚህ ድርጂቶች ውስጥ የሚሰሩ የውጭ ወገኖችን ጭምር ስም እስከ ማጥፋትና ዛቻ ድረስ የሚሄድ ሴራ ይጎነጉናሉ::

እኒህ  ልማትና  ብልፅግና የማይጥማቸው አካላት ስራ መስራትን ትተው ነጋ ጠባ የአገራችንን ስም በማጥፋት በየመንግስታቱ ጽ/ቤት ሲጮህ ይውላሉ:: በየሚኖርበት አካባቢ ያገኙትን የዜግነት መብት በመጠቀም አገራችን ጥቅም የሚጎዱ ጉዳዮችን በመንቀስ «እትዮጵያን አቃብሩን» ምህላ በማቅረብ በተጠማኝነት የተቀበሏቸውን የውጭ ዜጎች ግራ ያጋባሉ::

በአገሪቱ የተለያዩ ክልል አሰተዳደሮች ተዋቅረው የሚያደርጉትን የራስን ጉዳይ በራስ የማስተዳደር ህገመንግስታዊ መብት መልኩን በመለወጥ በኢትዮጵያ ህዝብን የሚያጫርስ ቦንብ እየተቀበረ ነውና ኑ እርዱን በማለት ሲያምታቱ ይውላሉ::
የአትዮጵያ መንግስት በግንቦት/97 እንከን የለሽ ምርጫ ለማካሄድ የጀመረውን የዳበረ ዴሞክራሲን የመገንባት መጠነ ሰፊ እንቅስቃሴ ይሄው በውጭ የሚገኝ አክራሪ ፖለቲከኛ የምርጫው ግብ እንዲለወጥ የተወሰነ የህ/ስብ ክፍልን በማነሳሳት መንግስትን ለመገልበጥ ያለመ ተግባር እንዲከናወን አጥብቆ ሰራ::በለኮሰው እሳትም የህዝብ ሀብት ወደመ::የወገኖቻችን  ህይወት እንዲጠፋ ምክኒያት ሆነ:: በወቅቱ መንግስት ጣልቃ ገብቶ ችግሮችን ለማበረድ ባይችል ኖሮ የጥፋቱን መጠን ለመገመት ይከብድ ነበር::ነውጠኛው ክፍል በዕቡይነት  የለኩሰው እሳት ተቀጣጥሎ የጎዳቸውን ወገኖችን  ጋሻ  በማድረግ የሰባዓዊ መብት ተቆርቋሪና ተሟጋች ሆኖ ለዚሁ አላማ የተቋቋሙ አለም አቀፍ ድርጂቶችንና ስብስቦችን በመማጠን አመለካከታቸውን በመበረዝ ላይ ይገኛሉ::



Bi-monthly news bulletin prepared by the Consulate General of Ethiopia
3460 Wilshire Blvd # 308  Los Angeles, CA 90010
Tel: 213 365 6651  Fax:213 365 6670 info@ethioconsulate-la.org
www.ethioconsulate-la.org

የጥላቻ ፖለቲካ አራመጁ የዲያስፖራ ጥቂት ክፍል ኢትዮጵያን ለመጉዳት ይሁነኝ ብሎ ከያዘው የመርገምት ሥራ አንደኛው ደግሞ በአሜሪካ የኮንግረስና ሴኔት ም/ቤቶች እንዲፀድቅለት የሚሯሯጥበት «ህግ» ነው:: ይህ በተለያየ ጊዜ ስሙን በመቀያየር የተነደፈው ህግ ምን ይሁን ምን አላማው ኢትዮጵያን ለማራከስና የአሜሪካ መንግስት ለአገራችን የሚሰጠውን ዕርዳት ለማቆም፣ በሁለቱ ወዳጅ አገሮች የተጀመረው በጎ ግንኙነት እንዲሻክር ከበጎ መንፈስ ሳይሆን ከንቀት፣ ዝቅ አድርጎ ከማየትና እናዋርዳቸው ከሚል መንፈስ የሚመነጭ ነው::

ቀደም ብሎ H.R **5680** የሚል ረቂቅ እንዲወጣ በማድረግ የኢትዮጵያንና የአሜሪካን ህግ አውጭ ም/ቤት ግንኙነት ለመመበረዝ የተደረገው ሙከራ፣ ጉዳዩን በውል በተረዱ ወገኖችና አገር ወዳድ በሆኑ ኢትዮጵያውያን ርብርብ ሊቆም ቢችልም፣ዘንድሮ ደግሞ ለተመሳሳይ ዓላማ ስሙን ቀይሮ H.R 2003 በሚል ስያሜ የኢትዮጵያን ሕዝብ ማቅ ለማልበስና አንገት ለማስደፋት ሽርጉዱን ተያይዘውታል::

በአጠቃላይ በዚህ ህግ ጀርባ በሰላማዊና ዴሞክራሲአዊ መልክ ትግል ማካሄድ የተሳናቸውና የማይችሉ፣በሀቀኛ ውድድር ሳይሆን «በህግ ረቂቅ» ስም በጓሮ በር የስልጣን መንበርን ለመቆናጠጥ የሚሹ፣ አገራችን በልፅጋ ማየት የማይፈልጉ ሀይላት፣አገራችን የምትከተለው መተክላዊና ለማንም ባርነት ያላደረ የውጭ ግንኙነታችን መርህ የሚያበሳጫቸው ክፍሎች፣አገራችን ተዳክማና አቀርቅራ ማየት የሚፈልጉ ወገኖች ይገኛሉ:: በዚህ ህግ እትዮጵያን እናግዛለን የሚሉ ወገኖችም ካሉ ይህ አካሄድ ከባህላችን ጋር የሚጣረስ በመሆኑ ከቶውኑም በግንኙነታችን ላይ ጠባሳ የሚጥል እንጂ ግንኙነታችን የሚያጠናክር አይደለም እንላለን:: የዚህ ህግ ግብ አገርን አዳክሞ የባዕዳን መፈንጫ ለማድረግ ነው::

የኢትዮጵያ መንግስት ከውጭ አገራት ጋር የሚኖረው ግንኙነት የአገሪቱን ጥቅምና የብሄራዊ ደህንነታችን መሰረት ያደረገ መሆን እንዳለበት በእምነት ብቻ ሳሆን በተግባር ያረጋገጠ መንግስት ነው:: ስለዚህም ከተባበረው የአሜሪካ መንግስት ጋር የሚኖረን ግንኙነት የሁለቱን አገሮች የጋራ ጥቅም መነሻ አድርጎ የሚከናወን እንጂ ወደ አንድ በኩል ያጋደለ የአዛገርና የአሽከር እንዲሆን ከቶውንም አይታሰብም:: በምንም መልክ የአገራችን ዘላቂ ጥቅም የማያረጋግጡ ጉዳዮችን የኢትዮጵያ መንግስት በማንም ጫና እንደማይቀበል ከአሁን በፊት ባከናወናቸው አለም አቀፍ የግንኙነት ሂደቶች አስመስክሯል::



**Bi-monthly news bulletin prepared by the Consulate General of Ethiopia**
**3460 Wilshire Blvd # 308 Los Angeles, CA 90010**
**Tel: 213 365 6651 Fax:213 365 6670 info@ethioconsulate-la.org**
**www.ethioconsulate-la.org**

## ሰሞነኛ

በመሆኑም የአሜሪካና የኢትጵያ ህዝቦች  የቆየና  ነባር የወዳጂነት ግንኙነት በዓለም አቀፍ ሁኔታ በተደቀኑ ትብብርን በሚሹና መርህን በተንተራሱ  ጉዳዮች ይበልጥ እየደመቀ የሚመጣ እንጂ የሚቀዘቅዝ አይሆንም:: በተለይም አገራችን ድህነትንና ኃላቃርነትን ለማስወገድ ግብ ግብ በያዘችበት በአሁኑ ወቅት እንደ አሜሪካ ያሉ የበለፀጉ አገሮች የሚያደርጉልን ዕገዛ ችላ የሚባል አይደልም:: ጠላቶቻችን የሚፈልጉትም ይህ በጎ መረዳዳትና መደጋገፍ ተቋርጦ የአገራችን እድገት ተደናቅፎ ማየትን ነው::

ስለዚህ ለአገራችን ደጉንና በጎወዎን  የምንመኝ ወገኖች ይህን ከውርደት በስተቀር አንዳች ጠቀሜታ የሌለውን ረቂቀ ህግ ለማስቆም ለኢትዮጵያና ለህዝቦቿዋ ፍቅርና ከበሬታ ካላቸው  ዕልፍ አዕላፍ አሜሪካውያን ወዳጆች ጋር በጋራ መስራት ይኖርብናል::በሁለቱ አገሮች መካከል አሁን የሚታየውን መልካም ግንኙነት እያዳበረ እንጂ ጥላሸት እየቀባ የሚሄድ ሥራ ሁሉ የማይጠቀም መሆኑን አበክረን መግለፅ ይገባናል::ይህን ማድረግም የአገርን በጎ ገፅታ የመገንባት ለመልካም ስማችን ጥብቅና የመቆም አካል ነው::



**Bi-monthly news bulletin prepared by the Consulate General of Ethiopia**
**3460 Wilshire Blvd # 308  Los Angeles, CA 90010**
**Tel: 213 365 6651  Fax:213 365 6670 info@ethioconsulate-la.org**
**www.ethioconsulate-la.org**